# አቶ ተክሌ የሻው የአማራ ህልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ሊቀመነበር ኢትዮጵያ ገቡ

June30 2018



አቶ ተክሌ የሻው የአማራ ህልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ሊቀመነበር ኢትዮጵያ ገቡ

የሞረሸ ለወገኔ የአማራ ሲቪክ ማህበር መስራች አና የአማራ ህልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ተክሌ የሻው ኢትዮጵያ ገቡ፡፡

አቶ ተከሌ በውጭ አገር ሆነው ሞረሽ የሚባለው የሲቪክ ድርጅት በመስረት በአማራ ህዝብ ላይ እየደረሰው ያለው ሰቆቃ፣ ግድያና መፈናቀል መረጃዎች በመሰብሰብና ለህዝብ በማሳወቅና እንዲሁም ለተጎዱት ወገኖቻችን በድርጅታቸው በሞረሽ ወገኔ ስም በመርዳት ከፈተኛ አስተዋጾ እያደረጉ ይገኛል፡፡ አቶ ተከሌ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት አሁን በሃገራችን ያለውን የለውጥ እንቅስቃሴ ሂደት በአካል ለማየትና በአገር ቤት ከሚገኙ የአማራ ና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ጋር ውይይት ለማድረግ ነው፡፡

አቶ ተከሌ የሻው ወደ ኢትዮጵያ ከመመለሳቸው በፊት የአማራ ክልል መንግስት በውጭ የሚገኙ የአማራ ድርጅቶችን ወደ ሃገር ቤት መጥተው እንዲታገሉ ለማግባባት ከተላከ የብአዴን ከፍተኛ አማራሮች ጋር ረጅም ግዜ የፈጀው ውይይት እንዳደረጉ ከአማራ ድምጽ ራዴዮ ጋር ባደረጉት ቃልለመጠየቅ ገለጸዋል፡፡